# የትምህርት ስድስት

## የሙከራ (የመወያያ) ጥያቄዎች

«በወንጌልም ማኅበርተኛ እሆን ዘንድ ስለ ወንጌል ሁሉን አደርጋለሁ» (1ኛ ቆሮ. 9፡23)።

1. ማንኛውም ሥራ ያለመማሪያ እንደማይሠራ ግልጽ ነው። የአገልግሎት መማሪያ ናቸው የምትላቸውን አብራራ።

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

2. ጸሎት ለአገልግሎትህ እንዴት መማሪያ ሊሆን እንደሚችል ግለጽ።

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

3. የእግዚአብሔር ቃል ለአገልግሎትህ እንዴት መማሪያ ሊሆን እንደሚችል አብራራ።

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

4. መንፈስ ቅዱስ ለአገልግሎትህ በመማሪያነቱ ያለውን ጠቀሜታ ግለጽ።

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

# ትምህርት ሰባት

# የአገልግሎት ዋጋ

- አገልግሎትህ በፈታኝና በአስቸጋሪ ሁኔታው ውስጥ ካሳለፈው ለታላቅ በረከትነት እያሰናዳህ ነው!
- ለማን መንግሥት እንደምትሠራና ዋጋህን በየት እንደምትከፈል አትርሳ!

<u>ዓላማ</u>፡- አገልጋዩ በሚያገለግልበት ወቅት አገልግሎቱ የሚያስከፍለውን ዋጋና የሚያሽልመውን ሽልማት ለማሳየት ነው። መዝ. (69)፡4-12

የአገልግሎትን ዋጋ ከሁለት አንጻር ማየት ይቻላል፡-

ሀ) አገልግሎት ዋጋ ያስከፍላል።

ለ) አገልግሎት ዋጋ ያስገኛል (ያሸልማል)።

<u>መግቢያ</u>

በዙሪያችን የምናውቃቸው ጉዳዮች ሁሉ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ዋጋ ማስከፈላቸው ወይም ዋጋ ማስገኘታቸው አይቀሬ ነው። እኛም በእነዚህ ሁለት ጉዳዮች ዙሪያ ጥቂት ነጥቦችን እንመለከታለን።

ሀ) አገልጋይ አገልግሎቱ ለሚጠይቀው መሥዋዕትነት የተዘጋጀ መሆን ይኖርበታል (ማቴ. 16፡21)።

- አገልጋይ በብዙ አስቸጋሪና ፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ በማለፍ ለሚያገለግለው ሕዝብ ታላቅ በረከት እንደሚሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ የምንረዳው እውነት ነው። በ1ኛ ዜና 21፡24-27 ስለ መሥዋዕት አቀራረብ በሚያመለክተው አሳብ ውስጥ ዳዊት እንዲህ ማለቱን እንገነዘባለን። ሕዝቡ ይዳን ይጠቀም እንጂ እኔ ዋጋ ከፍዬ መሥዋዕቴን ማቅረብ አለብኝ። ዋጋ ያልከፈልኩበትን መሥዋዕት አላቀርብም በማለቱ ዋጋ በመክፈል የሚቀርብ መሥዋዕት ምን ያህል አገልጋዩን የሚያሳርፍና የሚያረካ እንደሆነ እንማራለን።

❖ አገልግሎትህ በፈታኝና አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ካሳለፈህ ለታላቅ በረከትነት እያሰናዳህ ነው!

ለምሳሌ፥ በዓለማችን ላይ የሚገኙት ታላላቅ፥ አስደናቂና ማራኪ ሐውልቶች ሁሉ የጠራቢው መሮና መዶሻ ውጤቶች የሆኑትን ያህል፥ በልዩ ልዩ መከራዎች ወይም ፈተናዎች ተጠርቦና ተሞርዶ ያለፈ አገልጋይም አገልግሎቱ ማራኪ ሊሆን ይችላል።

## አገልጋይ ዋጋ ሊከፍል የሚችልባቸው ክልሎች፡—

1. አገልጋይ የሚገባውን ጥቅም(መብት) በውዴታም ሆነ በግዴታ የማጣት (የመነጠቅ) ፈተና ሊገጥመው ይችላል። ይህ ነጥብ አገልጋይ ሊያገኝ በሚመኘውና ወደ ፊት ተስፋ በሚያደርገው ጉዳይ ላይ ስለሚያጋጥመው ፈተና ጠቋሚ ነው። አገልጋይ ዋጋ ከሚጠየቅባቸው አንዱ ይህ ዓይነት ሁኔታ ነው። ይህ ደግሞ በቀደሙት ቅዱሳን አገልግሎት ዘመን ተከስቶ ነበር።

- ከእውነቶች መካከል እግዚአብሔር ላሳየንና ለገለጠልን ጉዳይ እና ለራእዮቻችን ስንል የምንጎዳባቸው ሁኔታዎች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ማመን አለብን። ለምሳሌ፥ ነህምያ ለአለቃ የሚገባውን ስንቅ አልሻም ነበር ብሏል (ነህ. 5፡15፥ 18፥19)።
  - ጳውሎስ፥ ለሐዋርያት የሚገባውን ማግኘት ስንችል አልከበድንባችሁም ብሏል (1ኛ ተሰሎ. 2፡5—8)።

የብዙ ቅዱሳን አገልጋዮችን የአገልግሎት ሂደት ስናጠና የምንማረው በአብዛኛው ማለት ይቻላል አገልግሎት ለእኛነታችን ጠቃሚ ከምንላቸው አንዳንድ ጉዳዮቻችን ሊያጎድልብን፥ ሊያሳጣንና ሊያስነጥቀንም እንደሚችል ነው። በዚህ ምክንያት ከሁለት አንዱን፥ ማለትም ወይ የአገልግሎታችንን አለያም የምቾታችንን ልንመርጥ ግድ ይሆናል።

2. አገልጋይ ያለውን የመነጠቅና የማጣት፥ በዚህም አኳያ ዋጋ የመክፈል ፈተናም ሊገጥመው ይችላል (1ኛ ነገሥት 19፡19፤ ሉቃስ 5፡27)። አንዳንዴ በአገልግሎታችን የሌለንንና ገና የምንመኘውን ማግኘት ቀርቶ ስለተጠራንለት ዓላማ ስንል ያለንንም እንኳ መሥዋዕት ማድረግ ግድ ሊሆንብን ይችላል። ለምሳሌ፥ በዕብ. 11፡24 በሙሴ ዘንድ የነበረው መሥዋዕትነት ተገልጾአል። እንደ ሙሴ በአገልግሎት ምክንያት በዓለም የነበረንን ጥቅም፥ ዝናና ክብር ልናጣ እንችላለን።

በ2ኛ ቆሮ. 11፡23—27 በጳውሎስ ዘንድ የነበረው መሥዋዕትነት ተጠቅሷል። ምናልባትም ንብረታችንን ልናጣ እንችል ይሆናል። ሌላው የአገልግሎት «ወንበር» ወይም ሥልጣን ሊሆን ይችላል። እኛም ጥቂት

ያልሆኑ ነገሮችን ለማጣት እንገደድ ይሆናል (ዕብ. 12፡4)። ይህም ጤናችንንና ነፍሳችንንም ሊያካትት ይችላል።

3. አገልጋይ ለአገልግሎቱ መስጠት ከሚጠበቅበት ጊዜ የተነሣ የራሱንና የቤተሰቡን አጠቃላይ ሁኔታ እንዳይጠብቅ እንኳ የሚከለክሉ ፈተናዎች ሊገጥሙት ይችላሉ። ሰይጣንም በሚታይና በማይታይ ሁኔታ ሁሉ ኋላቀር እየሆነ እንዳለ በማሳሰብ ሊፈትነው ይችላል። ፈተናውም ሥቃይ ይሆንበታል። ይህም የጊዜ ጉዳይ አገልጋይ ዋጋ ከሚከፍልበት መንገድ አንዱ መሆኑን አውቆ መሰማራት ይገባዋል። ይህም ስለተባለ ቤተሰቡን ከአቅሙ በላይ ባልሆነ ምክንያት ለማስራብ፥ ለማስጠማትና ተገቢውንም ኃላፊነቱን ላለመወጣት አገልጋዩ የሚገፋፋበት ሊሆን አይገባም። እርሱ ካልቻለ ለሌላ ለታማኝ ሰው አደራ ሊሰጥ ይገባዋል (1ኛ ጢሞ. 5፡4–8፤ ዮሐ. 19፡26)።

## <u>ማጠቃለያ</u>

አገልጋይ በአገልግሎቱ ምክንያት ብዙ ግልጽና ስውር ችግሮች ሊገጥሙት ይችላሉ። ነገር ግን በአንድ ፋብሪካ ውስጥ የሚሠራ ትጉሕ ሠራተኛ በፋብሪካው የማሽኖች ጩኸት ሳይወሰድ፥ ሳይደናገጥና ሳይረበሽ ሥራውን ብቻ አትኩሮ ይሠራል። አገልጋይም እንዲሁ በአገልግሎቱ ዙሪያ የሚገጥመውን የመከራና የፈተና ጩኸት ግምት ውስጥ ሳያስገባ፥ የአገልግሎቱ አንዱ ክፍል ዋጋ መክፈል መሆኑን በመገንዘብ ሊተጋ ይገባል።

ለ) አገልጋይ አገልግሎቱ ዋጋ ሊያስገኝለት ወይም ሊያስጠው እንደሚችል ማመንና ማወቅ አለበት (1ኛ ቆሮ. 15፡58)። «ስለዚህ፥ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ድካማችሁ በጌታ ከንቱ እንዳይሆን አውቃችኋልና...»። ማገልገልና ለእግዚአብሔር ፕሮግራሞች መድከም ፍሬ ቢስና ከንቱ አለመሆኑን እንረዳለን (ሚል. 3፡14)።

አገልጋይ ለአገልግሎቱ ዋጋ እንዳለው ማወቅ ብቻም ሳይሆን፥ ዋጋውን ከማን እንደሚያገኝም የተረዳ መሆን አለበት። <u>ለምሳሌ፥</u> በአንድ ወቅት በአንዲት አፍሪካ አገር ውስጥ ለ30 ዓመታት በሚሲዮናዊነት ሲያገለግሉ የቆዩ ባልና ሚስት ሚስዮናውያን አገልግሎታቸውን ጨርሰው ወደ አገራቸው ሲመለሱ ይጓዙበት የነበረው መርከብ ውስጥ የአገራቸው ዜጋ የሆነ የኦሎምፒክ ተወዳዳሪ አሸናፊ እየተመለሰ ስለነበር ታላቅ ፌሽታ በዚያ ሆኖ ነበር። ከዚያም አገራቸው ሲደርሱ ደግሞ የአገሪቱ ባለሥልጣናትና ብዙ ሕዝብ አቀባበል አደረጉለት። ይህንን ያዩት ሚሲዮናዊ በጣም ኀዘን ተሰማቸውና ባለቤታቸውን እንዲህ አሉአቸው፤ «አየሽ፥ እኔና አንቺ

30 ዓመታት ሙሉ ከአገራችን ወጥተን በማይመች መንገድ ሁሉ አልፈን አገልግሎታችንን አጠናቅቀን ስንመለስ ያለፌሽታ ጥሩ አቀባበል እንኳ የሚያደርግልን በሌለበት ነው የምንገባው።» ሚስትየውም ለባለቤታቸው እንዲህ ሲሉ ጥያቄ አቀረቡ፤ «ይህ ሹሞ የሮጠው ለማን መንግሥት ነው? አቀባበልስ የሚያደርግለት የማን መንግሥት ነው?» ቢሏቸው፥ የአሜሪካን አሉ። «እንግዲያስ አንተና እኔ የሮጥነውና ያገለገልነው ለየትኛው መንግሥት ነው? አቀባበልስ የምንጠብቀው ከየት ነው?» ቢሏቸው ወደ ልባቸው ተመለሱ ሲባል ሰምቻለሁ። ስለዚህ አገልጋዮች ለማን እንደምንሮጥ ሊጠፉብን አይገባም። የአገልጋይ ዋጋው በእግዚአብሔር እጅ ነው!

❖ በእርግጥ የአገልጋዩ የአገልግሎት ዋጋ አንዳንዴ በሰማይ ብቻ የሚጠበቅ ላይሆን ይችላል፤ በምድር የምንከፈልበትና በሰማይ ደግሞ ሙሉ ለሙሉ የምንሸለምበት ነው (ሉቃስ 18፡30)።

ማንኛውም ሠራተኛ በሥራ ጊዜው ወይም በወር መጨረሻ ላይ ደመወዙን ለመቀበል ወደ ደመወዝ ከፋዩ እንደሚፈጥን ሁሉ፥ አገልጋይም በአገልግሎቱ ፍጻሜ ዋጋውን ከከፋዩ ለመቀበል ዕድል እንዳለው ከቅዱስ ቃሉ መረዳት ይቻላል፤ (2ኛ ጢሞ. 4፡6፤ ዕብ. 6፡10፤ ራእይ 22 ይመልከቱ።)

❖ ዋጋዎች ሆነው ከተጠቀሙልን መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡–

1. በእግዚአብሔር ዘንድ ለአገልጋዩ መከበር ይሆንለታል። (ዮሐ. 12፡26 ይመልከቱ።) እውነተኛ አገልጋይ በዘመኑ ሁሉ የከበረ ነው። «. . . አሁን ግን እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡– ያከበሩኝን አከብራለሁና» (ዮሐ. 5፡44፤ ዕብ. 5፡4፤ ዳን. 12፡3፤ 1ኛ ሳሙ. 2፡30ን ይመልከቱ።) «. . . ብዙ ሰዎችን ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ።»

2. ወደ እግዚአብሔር ደስታ መግባት አንዱ የአገልጋይ ዋጋ ነው (ማቴ. 25፡21–23)። ክፍሉ በመክሊታቸው ባተረፉትና በከሰሩት ባሪያዎች ዙሪያ የተነገረ አሳብ ሲሆን፥ ለታመኑት ትልቅ ብድራት መሆኑን ያስተምረናል።

❖ አንድ እውነት አለ፤ ይህን ደስታ ማንም በምን ዓይነትም ሊገልጸውና በምንም ሊመስለው አይችልም። ደስታው ግን አገልጋዩ በእውነተኛ አገልግሎቱ ዙሪያ ሆኖ፡–

❖ በተነጠቃቸው መብቶች ምክንያት፥

❖ አገልጋይ ለምን እንደተጠራ ካላወቀ እንዴት እንደሚኖር አያውቅም።

* በነገሮቹ ወይም በምኞቶቹ ያለመሳካት ምክንያት፥
* በኀዘኖቹ ወይም በጉድለቶቹ ምክንያት፥
* በሕመምና በመሥዋዕትነት ምክንያት እንኳ ያጣችውን ደስታዎች ሊተኩለት ወይም ፍጹም ሊክሱት የሚችሉ ደስታዎች መሆናቸውን ግን በድፍረት ማመን ይቻላል (ራእይ 21፡4–7)። ጌታ ይባረክ! አሜን

3. ጌታ ለባሪያዎቹ ወይም ለአገልጋዮቹ ያዘጋጃቸው ልዩ ልዩ ሽልማቶች በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱት የአገልጋዩ ዋጋዎች ናቸው።

በተለይ ራእይን ስናጠና «እንዲህ እሰጠዋለሁ. . . እሰጠዋለሁ!» የሚሉት አባባሎች አገልጋዩ ላሳየው ትጋትና ታማኝነት ዋጋ እንዳለው ጠቋሚ ናቸው (ራእይ 2፡17)። «እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ» (ራእይ 2፡10)።

አገልጋዩ በአገልግሎቱ ሂደት ውስጥ፦

* ለተዋረደባቸው ጉዳዮች የክብር አክሊል (1ኛ ጴጥ. 5፡14)፥
* በአሸናፊነት ለተመላለሰባቸው ጉዳዮች የድል አክሊል፥ ወዘተ... ይቀበላል።

«ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ» (ራእይ 3፡21)።

* የማይጠፋ አክሊል (1ኛ ቆሮ. 9፡25)፥
* የተስፋ አክሊል (1ኛ ተሰሎ. 2፡19)፥
* የጽድቅ አክሊል (2ኛ ጢሞ. 4፡8)፥
* የሕይወት አክሊል (ያዕ. 1፡12)፥

ጳውሎስ በዚህ ምክንያት እንዲህ ብሏል፦ «ለእኛም ሊገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ።» ይህንንም ያለው እግዚአብሔር ለአገልጋዩ ወደ ፊት የሚያስገኝለትን በሩቅ በማየት ይመስላል (ሮሜ 8፡18)። በማገልገላችን እዚህ እያለንም እንኳ ብዙ ብዙ ዋጋዎችን ወይም በረከቶችን ለማትረፍ ይቻላል።

* ታማኝ አገልጋይ በምድር አገልግሎቱ ዘመናት ውስጥ፦

1. በአገልጋዩ ሕይወት ውስጥ በማገልገሉ ምክንያት በዘመኑ ሁሉ መንፈሳዊ እርካታ መፈጠሩ አስደናቂ በረከት ነው።

2. በአገልግሎቱ ወደ ፊት የመዘርጋት፥ የተሻለ ለማገልገል መናፈቅና በመንፈስ መጋል፥ አገልግሎቱን እንዳላበቃና እንዳልጨረሰ የመቁጠሩ ስሜት በአገልጋዩ ሕይወት ያለ ትልቅ ዋጋ (በረከትን) ነው።

3. ለመልእክቶቻችን ወይም ለአገለገልንባቸው ርእሶች ታማኝ ሆኖ መገኘት መቻል በራሱ ትልቅ ዋጋ (በረከትም) ነው። ለምሳሌ፥ ስለ ፍቅር፥ ስለ ምስጋናና ስለ መገዛት ላገለገልንባቸው ርእሶቻችን ጠንቃቃ ሆኖ መገኘት ዋጋን (በረከትን) የማግኘት ያህል መሆኑን እምናለሁ።

ማጠቃለያ፤ አገልጋይ አገልግሎቱን ለማስኬድ አገልግሎቱ የሚጠብቅበትንም ሆነ ከአገልግሎቱ ጌታ የሚጠበቀውን ዋጋ ባለመዘንጋት፥ የሚጠበቅበትን ለመመለስ መሰናዳትና የሚጠብቀውን ተስፋ በማድረግ ለመመላለስ መትጋት ይገባዋል።

## የትምህርት ሰባት

## የሙከራ (የመወያያ) ጥያቄዎች

«ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቆጥራለሁ» (የሐዋ. 20፡24)

1. አገልጋይ ዋጋ ሊከፍል የሚችልባቸው ሁኔታዎች ምን ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ አብራራ።

________________________________________

________________________________________

________________________________________

2. ለአገልጋይ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሰው ከምናገኛቸውና የአገልግሎታችን ዋጋዎች ናቸው ከምንላቸው መካከል ጥቂቱን ግለጽ።

________________________________________

________________________________________

3. በትምህርት ሰባት መሠረት የአገልግሎታችንን በረከቶች ግለጽ።

4. ስለ አገልግሎት ዋጋ መክፈልና ዋጋ ማግኘት ያገኘኸውን ግንዛቤ ግለጽ።

# ትምህርት ስምንት

## የአገልግሎት ደረጃ (መጠን)

ዓላማ፡- በአገልግሎት ዙሪያ ምንም ዓይነት መበላለጥ ሁሉም አገልግሎት እኩል እንደሆነ ለማሳወቅ ነው።

የዛሬዋ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ከአገልግሎት ስጦታዎች አጠቃቀም አንጻር እንዴት ትስተዋላለች፥ የተመጣጠነ የአገልግሎት እንቅስቃሴ ይታይባታል ወይ?

<u>መግቢያ</u>

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት የአገልግሎት ዘርፎች የሚፈለገውን ያህል ተመጣጣኝና አመርቂ እድገት ያላሳዩባቸውን ልዩ ልዩ ምክንያቶች መጥቀስ ይቻላል። ይህን ቅርጽ የለሽ ሁኔታ በጥሩ ፍጥነት ታግሎ አገልግሎቶችን ወደ ተመጣጣኝ እድገት ለማምጣት ጥረት መደረግ ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹ አገልግሎቶች አገልጋይ አጥተው የቅጥር ሠራተኞች ሥራ ብቻ ሆነው ሊቀሩና ሊቆጠሩ ይችላሉ። ይህ ማለት እግዚአብሔር ከእነዚህ

አገልግሎቶች አንጻር በሰዎች ውስጥ ያስቀመጠውን ጸጋ ማሳጣት፥ ማዳፈንና ማስቀረት፥ እና ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ሙላት ማጉደል መሆኑንም አገልጋይ ልብ ማለት አለበት። ለምሳሌ፥ በአንዳንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የናታኒ አገልግሎት (የጽዳት አገልግሎት) በመባል የሚታወቀውና ብዙ ለእግዚአብሔር ክብር የቆሙ ሰዎች የሚገኙበት የአገልግሎት መስክ አንዱ ነው።

❖ ስለዚህ አገልግሎቶች ሁሉ በየአቅጣጫዎቻቸው ተጠናክረውና ተመጣጣኝ ሆነው የሚንቀሳቀሱበትን ልምድ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናንን ማስተማር አለባት።

በቤተ ክርስቲያን አንዱ አንዱን ሲያገለግል ሌላኛው ሌላውን የመሥራት ልምድ ማጎልበት ይገባል። ይህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ ነው ወደ ተመጣጣኝ የአገልግሎት አሰጣጥ የሚያመጣን። እያንዳንዱ ስጦታውን በተገቢው ጊዜ ለተገቢው ቦታ ማዋል መቻል አለበት።

1. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አገልግሎቶች እኩል ወይም ተመጣጣኝ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ቢያንስ የሚከተሉት ነጥቦች መታወቅና መከበር ይኖርባቸዋል።

አገልጋዩ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አገልግሎት ዓይነቶች (ዘርፎች) የሚያስተምረውን እውነት መረዳት ይኖርበታል (1ኛ ቆሮ. 12፡4−10፥ 28−30 ይመልከቱ።) በአካል ጥሩ ለውጥና እድገት ሊታይ የሚችለው አካል ሁሉ ተባብሮና ተቀባብሎ የመሥራት ኃላፊነቱን ሲወጣ መሆኑን መዘንጋት የለብንም።

- በአገልግሎቷ እውነተኛ ትብብርና ትስስር የማይገለጥባት ቤተ ክርስቲያን እድገቷ አስጊ ነው።


ከዚህም በመነሣት አገልጋዩ፡−

1.1 አገልግሎቶች ሁሉ እኩል አክብሮት፥ ተፈላጊነትና ዋጋ እንዳላቸው ማወቁ ትልቅ ጠቀሜታ አለው።

- የትኛው አገልግሎት ነው ከሁሉ የተሻለ ደረጃ ያለው?
- የትኛው አገልግሎት ነው ከሁሉ ጥሩ ሽልማት የሚያስገኘው? ተብለን ብንጠየቅ በእርግጠኝነት ደፍረን የምንመልሰው የለንም።

❖ በአገልግሎት ዓለም በራስ ያለ አገባብ መተማመንና ራስን ለማሳየት መጣር ለውድቀት መንደርደር ነው!

የአገልግሎቶች እውነተኛ አቀማመጥ እንደ ቀለበት ይመስለኛል። ይህም በአገልግሎቶች መካከል ምንም ዓይነት መበላለጥ ያለመኖሩን ጥሩ አድርጎ ሊገልጥ የሚችል ነው።




የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ተመጣጣኝ ሆነው የመገኘታቸው ምሥጢር እኩልነታቸውን ማመን ነው።

❖ አገልግሎት የመተጋገዝ ሥራ ነው፤ (2ኛ ዜና 29፡31 ይመልከቱ።)

<u>ለምሳሌ፣</u> በአንድ ፋብሪካ ውስጥ ተመርቶ የሚወጣ ልብስ በልዩ ልዩ ዓይነት ችሎታና ተሰጥኦ ባላቸው ሠራተኞች ትብብር ለዋጋ ይበቃል። በቤተ ክርስቲያን መድረክ የሚቀርቡ አገልግሎቶችም እንዲሁ ተቀናጅተው ሲፈጸሙ ውጤት እንደሚኖራቸው መታወቅ አለበት። በተጨማሪም በአንድ ትልቅ ቤት ውስጥ የልዩ ልዩ ክፍሎች ዕቃ እንዳለና ለባለቤቱ እኩል ጠቀሜታ እንደሚሰጡ ማሰብ የአገልግሎት ዘርፎችን በእኩልነት ለማየት ጠቃሚ ነው።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ሰዎችን ስናስተውል ግን የተወሰኑ የአገልግሎት ዘርፎች ብቻ ዋጋ አላቸው የተባሉ ይመስላል። በመሠረቱ ይህ የተሳሳተ ሩጫ ማለት ነው።

❖ ውድ ወገኖች፣ እኛ አገልጋዮች ማወቅ ያለብን የሮጠ ሁሉ ተሸላሚ እንደማይሆንና ያለ ቦታችን ብናገለግልም ዋጋ እንደማይኖረን ነው። የሚፈለገው በተመደቡበት የአገልግሎት መስመር ኃላፊነትን በጥሩ ሁኔታ መፈጸም መቻል እንጂ ሽልማቱ እንደሆነ ያው አንድ ነው።

በዓለማችን እንኳን ስናይ በየትኛውም ምድብ ሮጦ አንደኛ የወጣ ተወዳዳሪ (ስፖርተኛ) የሚሸለመው ሜዳሊያ አንድ ዓይነት መሆኑን እናውቃለን።

- ማራቶን ሮጦ አንደኛ የወጣ የወርቅ ሜዳሊያ ይሸለማል።
- 10,000 ሜትር ሮጦ አንደኛ የወጣውም የወርቅ ሜዳሊያ ይሸለማል።
- 5,000 ሜትር ሮጦ አንደኛ ለወጣውም የወርቅ ሜዳሊያ ይሸልሙታል።
- 1,000 ሜትር ሮጦ አንደኛ የወጣ ስፖርተኛም እንዲሁ የወርቅ ሜዳሊያ ይሸለማል።
- 400 ሜትር ሮጦ አንደኛ የወጣ ተወዳዳሪም ሽልማቱ የወርቅ ሜዳሊያ ነው።

<u>ለምሳሌ፥</u> በማጽናናት፥ በማስተማር፥ በማስተናገድ፥ በመዘመር፥ በማጽዳት፥ በመጎብኘት፥ ወዘተ... የሚገኘው ዋጋ አንድ ነው።

1.2 ማንኛውም አገልጋይ አገልግሎትን ስለወደደና ስለተመኘ ብቻ በአገልግሎት ሊሳተፍ (ሊሰማራ) እንደማያስፈልግ ግን ማወቅ ጠቃሚ ነው።

እግዚአብሔር እኛን የሚፈልገው ወደሚወደው ሊያሰማራን እንጂ እኛ ወደምንወደው ልንሰማራ አለመሆኑን መረዳት ይገባል። እርግጥ አገልጋይ በአገልግሎቱ ውስጥ ያለው ምኞት እከሌ ተብሎ መጠራትና መከበር ከሆነ ወይም መሻቱ ታላቅ ሆኖ መታወቅ ከሆነ፥ እርሱን ወደሚፈልግበት ለማድረስ ለእግዚአብሔር አስቸጋሪ ሊሆንበት ይችላል (ኤፌ. 4:7)። አገልጋይ ማወቅ የሚኖርበት ሌላው ነገር ያለቦታው በሚሰጠው አገልግሎት ማግኘት ውጤት አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል ነው (የሐዋ. 6:1–6 ይመልከቱ።)

❖ አንድ የእግዚአብሔር ሰው ያለው ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። «ብዙ ዶክተሮች ቢሰባሰቡም አንድን የፈረሰ ድልድይ ሊሠሩ አይችሉም፤ አንድ ኢንጂነር ግን ጥሩ አድርጎ ለመሥራት ይበቃል» ብሏል።

- ያለ ቦታና ያለ ስጦታ በማየትና በመስማት ብቻ ለማገልገል መሞከር ጉዳትም ያስከትላል (የሐዋ. 19:11–16ን ይመልከቱ።) መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚጠቁመን በአስቄዋ ልጆች ላይ የሆነውን ትምህርት በድጋሚ ብናነሣው ጥሩ ነው።

- ስለዚህ አገልጋዮች ለማገልገል ቦታችንን (ስጦታችንን) በማወቅ ጌታ ወደሚያስማራን አገልግሎት በፈቃደኝነት ለመሰማራት የጨከንን መሆን አለብን።

1.3 በመጨረሻም አገልግሎቶች ሁሉ በአንዱ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋና እርዳታ የሚከናወኑ የጌታ ሥራዎች እንጂ፥ በሰው የተለየ ብቃትና ችሎታ ምክንያት መሰማሪያ አለመሆናቸውን አገልጋይ መረዳትና ማስረዳት አለበት።

❖ በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ የሚታረሙና ሊታረሙ የሚገባቸው አመለካከቶችና አባባሎች አሉ።

<u>ለምሳሌ</u>፥ ከጽዳት ወደ ዘማሪነት ነው መምጣት ያለብኝ።

- ከወንጌላዊነት ወደ መጋቢነት ነው መምጣት ያለበት።
- እኔ ይህን ስለማልችል ጽዳት ይሻለኛል።
- እኔ ይህን ስለማልችል በጸሎት ማገልገል ይሻለኛል።

❖ አንዳንዴ እንደ እነዚህ ያሉትን አባባሎች የምንጠቀመው ራሳችንን ትሑት ያደረግን መስሎን ይሆናል። ይሁን እንጂ፥ እነዚህን የመሳሰሉት አባባሎችና አመለካከቶች ፍጹም መታረም ያለባቸው፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑና ትልቅ ስሕተት የሞላባቸው መሆኑን መገንዘብ አለብን። የጌታ ሥራ የሚሠራው በሰው ችሎታ፥ ብቃትና ማንነት አይደለም። ይልቅ አገልጋይ አገልግሎቶች ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ እኩል ተቀባይነትና እኩልም ጠቀሜታ እንዳላቸው በማመን ስፍራውን ከአገልግሎቱ ባለቤት ጋር በመመካከር ለይቶ በዚያ መስመር ለመሮጥ መሰናዳት ይገባዋል።

❖ ይህ የአገልግሎት አለመበላለጥ ምሥጢር የገባቸው ትልልቆቹ፥ የተማሩና ባለጠጎች የሆኑ ሁሉ ጌታ ባሳያቸው ሲያገለግሉ ይስተዋላሉ።

አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ የአገልግሎት ዘርፎች ሥራ ለሌላቸውና ጊዜ ለተረፋቸው የተሰጡ ይመስላሉ። በተለይ ጽዳት፥ ጸሎትና መስተንግዶ በአንዳንድ ቦታዎች (በቤተ ክርስቲያን) ዘንድ ጥሩ ግምት የተሰጣቸው አይመስሉም! ይህ ደግሞ በፍጥነት መታረም ይገባዋል።

❖ መፍትሔውም ከእኛ ምርጫና ምኞት መለየትና ጌታ ወደሚያስማራን የአገልግሎት መስክ ለመሰማራት ፍጹም ፈቃደኛነት ማሳየት ነው።

የጌታ ሥራ ይብዛላችሁ ስለ ተባለ የጌታን ሥራ በብዙ መልኩ መሥራት ግን ይቻላል።

## 2. የአገልግሎት ስጦታችንን ለመለየት የሚረዱን አሳቦች

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ቁጥር ያላቸው የአገልግሎት ዓይነቶች እንደ መኖራቸው መጠን እያንዳንዱ ምእመናን ትክክለኛውን የአገልግሎት ስጦታ (ስፍራ) ለይቶ እንዲያውቅ ትምህርትና ምክር መስጠት አስፈላጊ ነው።

❖ የአገልግሎት ስፍራን ለማረጋገጥ እነዚህን ነጥቦች ብንከተል ውጤት ወደምናተርፍበት ቦታ መድረስ ይቻላል።

2.1 አገልጋዩ ጥሩ ውጤት ሊያሳይና ሊያስገኝ የሚያስችለውን የአገልግሎት መስክ ለይቶ ለማወቅ በጸሎት ራስን ማዘጋጀት።

- አገልጋዩ ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት ጌታ ለየትኛው የአገልግሎት ስፍራ እንደሚፈልገው በጸሎት ማረጋገጥ አለበት።

2.2 ስለ አገልግሎት ጠቃሚና አነሣሽ የሚሆኑ ትምህርቶችንና ሥልጠናዎችን መውሰድና ልዩ ልዩ ጽሑፎችን ማንበብና የተረዱትን እውነት ለመከተል መወሰን።

2.3 ስጦታዬ ነው፥ እግዚአብሔርም ወደዚህ አመላክቶኛል ብለህ ያመንክበትን አገልግሎት መለማመድና በመንፈሳዊ ዝንባሌህ ውስጥ መንቀሳቀስን አትፈራ።

2.4 በትሕትና መንፈስ እየተንቀሳቀስክበት ባለው አገልግሎት ውስጥ ምን ያህል ውጤታማ እንደሆንክ ራስህን በራስህ ለመገምገምና ከዚህም የተነሣ ለመቀጠል ወይም ለማቆም የጠበቀ ውሳኔ ለመውሰድ።

2.5 ስለ አንተ ጥሩ አመለካከት እንዳላቸው የምትገምታቸውን የቅርብና በሳል የሆኑ አገልጋዮች ስለ አንተ አገልግሎትና አገልጋይነት የሚታያቸውንና የሚሰማቸውን ግልጽ አስተያየት እንዲሰጡህ ለማድረግ፥ ያንንም ለመስማትና ለመቀበል ወስነህ እና በበጎ ሕሊና ተሞልተህ መጠይቁን አቅርብ።

2.6 ጥሪዬ ነው ለምትለው የአገልግሎት መስክ የጊዜ፥ የእውቀት፥ የብቃትን፥ የጉልበት፥ የአቅም፥ ወዘተ... ጥያቄ ለሚጠይቅህ ምን ያህል በቂ ምላሽ ለመስጠት እንደምትችል እርግጠኛነትህን ፈትሽ።

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ከአገልጋዩ የሚጠብቀው እርሱ ያከበረውን አክብሮ፥ የተቀበለውን ተቀብሎ በማስተናገድ ጥሪውን የሚፈጽምበትን ስፍራ ይዞ በሚንቀሳቀስበት የአገልግሎት መስክ ከሌላው ያላነሰ ወይም ያልበለጠ ክብር፥ ጸጋ፥ ብቃትና ዋጋ ባለው መልኩ እንደሚያገለግል በመረዳት ማገልገል እንደሚኖርበት ነው። በዚህ ዓይነቱ ሁኔታም እግዚአብሔር እንደሚደሰት፥ አገልጋዩም እንደሚባረክና አገልግሎቱም የተሳካ እንደሚሆን ማመን ከአገልጋዩ የሚጠበቅ ነገር ነው።

# የትምህርት ስምንት

## የሙከራ (የመወያያ) ጥያቄዎች

❖ «የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው፤ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው... (1ኛ ቆሮ. 12፡4-6)።

1. አገልግሎቶች በሙሉ እኩል ተመጣጣኝ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ መታወቅና መከበር ያለባቸውን ነጥቦች ግለጽ።

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

2. አገልጋይ የአገልግሎት ስጦታውን ለመለየት ከሚረዱት አሳቦች ጥቂቶቹን በማብራራት ጻፍ (ግለጽ)።

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

3. ሁሉም አገልግሎቶች ተመጣጣኝ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ መደረግ አለባቸው ብለህ የምታስበውን አብራራ።

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

# ትምህርት ዘጠኝ

# የአገልጋይ ችግሮች

ዓላማው፦ አገልጋይ በአገልግሎት ሂደቱ ወቅት ሊገጥሙት የሚችሉትን ችግሮች ለማሳየት ነው።

መግቢያ

በአለፉት አጠቃላይ ነጥቦች ውስጥ አልፎ የሚያገለግለው አገልጋይ በውስጡ ከሚፈጠሩ ወይም በዙሪያው ከሚነሡ ገጠመኞች የተነሣ ችግሮች ሊኖሩበት እንደሚችሉ ሁሉም ሊያውቀው የሚገባ ሲሆን፥ የችግሮቹም መንሥኤዎች ከብዙ በጥቂቱ የሚከተለውን ይመስላሉ፦

ሀ) የአገልጋዩ የግል ችግሮች

1. ጥሪውን እንደሚገባ ያለመገንዘብ

- አገልጋይን በግሉ ከሚገጥሙትና ፈታኝ ከሚሆኑበት ችግሮች አንዱ ለምን? እንዴት? ከየት? ለየት? እንደተጠራ የመዘንጋት ወይም ግንዛቤን የማጣት ችግር ሊሆን ይችላል። ጳውሎስ «ዴማስ የአሁኑን ዓለም ወዶ ትቶኛልና» (2ኛ ጢሞ. 4፥9) ይላል። ለመሆኑ ዴማስን ምን ነካው? ምን ችግር ገጠመው? ለምን? እንዴት ተጠርቶ ነበር? እኛስ ዛሬ ለምን እንደ ተጠራን ተገንዝበናልን?

«... በጌታ የተቀበልኸውን አገልግሎት እንድትፈጽመው ተጠንቀቅ በሉልኝ» (ቆላ. 4፥17)። ይህ በአንድ ወቅት ከጳውሎስ ጋር በወንጌል አብሮት ወታደር (አገልጋይ) ለነበረ ሰው የተሰጠ ማሳሰቢያ ነው።

- ከጥቅሶቹ የምንማረው ጳውሎስ ለምንና እንዴት እንደተጠራ ማሰቡን (መገንዘቡን) እንጂ ግራ ግራ መጋባቱን አይደለም።

❖ አገልጋይ ጥሪውን እንደ ጳውሎስ በግንዛቤ ሊያስተናግድ እንጂ ግራ ሊጋባ አይገባውም።

2. አገልጋይ በግል ሕይወቱ አንዳንዴ በጥርጥር ማዕበል የመገፋት ችግር ሊገጥመው ይችላል። ለዚህም እንደ መረጃ መጽሐፍ ቅዱስ ያቀየልንን ምሳሌዎች ብናይ፦

- ጴጥሮስ በባህር ላይ በእግሩ ጉዞ ከጀመረ በኋላ የመጠራጠሩ ስስተት፤

- የቶማስ የጌታን ችንካር ካልነካሁና ካላየሁ አላምንም ማለት (ዮሐ. 20፥25)።

- በሉቃስ 1፡18-19 እንደተጠቀሰው ሚስቱ ካህኑ ዘካርያስም ስለ መውለዷ ይህ ፈታኝ ችግር ገጥሞት ነበር።

- በሉቃስ 24፡37 እና 38 ላይ እንደምንረዳው ደቀ መዛሙርትም በጌታ ትንሣኤ ጥርጥር ገብቶባቸው ነበር። እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች ብዙ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል።

- አገልጋይ ጌታው የተናገረውን ወይም የገባለትን የተስፋ ቃል የሚያዘናጋና በጥርጥር ምድረ በዳ ላይ የሚያንከራትት ችግር ሊገጥመውም ይችላል።

❖ ይሁን እንጂ ከእነዚህ ቅዱሳን ታሪክ እንደምንረዳው እጃቸውን ለጌታ በመስጠት ታሪካቸው የተቃና መሆኑን በመረዳት እንዲህ ያለ ማዕበል ሲገፋን እጃችንን ለጌታ ማስረከብ ይጠበቅብናል።

3. በአገልጋይ ዘንድ አልፎ አልፎ የአለመታዘዝን መንፈስ የማስተናገድ ችግር ሊከሰት ይችላል (ዘኁልቁ 20፡10፤ 1ኛ ሳሙ. 15፡1)።

በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር የፈቀደውን ብቻ ሳይሆን አንዳንዴ አገልጋይ በአገልግሎቱ የራሱን መሥዋዕት አቅራቢ ይሆናል። ይህ ዓይነቱ ያለመታዘዝ ችግር ሲውል ሲያድር ከሌሎች ጋር ተግባብቶና ተቀናጅቶ ለማገልገልም ችግር ሊፈጥርበት ይችላል።

❖ ይህ ዓይነት ችግር ሳይፈጠር በጥሩ ፍጥነት ወደ መታዘዝ በመምጣት እንደ ነቢዩ ዮናስ ለፍሬ መብቃት ይኖርበታል።

4. አገልጋዩ እንደ ማንኛውም ሰው በልዩ ልዩ ምክንያቶች፥ በአካሉ ላይ የተለያዩ ችግሮች ሊገጥሙት ይችላሉ፤ (2ኛ ቆሮ. 11፡27፤ ዮሐ. 4፡6፤ ዘጸ. 18፡13-18)። እነዚህ በልዩ ልዩ ምክንያት በአካሉ ላይ የተከሰቱ ችግሮች ሌላ ችግር ሊያስከትሉበትም ይችላሉ። ለምሳሌ፥ መሰላቸት፥ ራስን መኮነን፥ ተስፋ መቁረጥን፥ ወዘተ...።

❖ በየዘመኑ የተነሡ አንዳንድ ቅዱሳን በዚህ ዓይነት ፈታኝ ሕይወት በጽናት ማለፋቸውን በመረዳት እኛም በመጽናት መቆም ይኖርብናል።

5. አገልጋይ በአገልግሎቱ ጊዜ የግል መሠረታዊ ፍላጎቶችን ያለማሟላት ችግር ሊገጥመው ይችላል (መዝ. 73፡1)። እንዲህ መሆኑ ደግሞ አገልጋዩን ወደ አላስፈላጊ ራስ ወዳድነት ሊመራው ይችላል። በተጨማሪም ራሱን ብቻ አገልጋይና አስተናጋጅ ያደርገው ይሆናል (ሕዝ. 34፡1-16)።

❖ እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ ማሰብ የሚኖርብን ሁሉን አጥተን ብቻ ሳይሆን ሁሉን ትተን ጌታን ለመከተልም እንደተማርን ነው። (ሉቃ. 5፡27)።

6. አገልጋይ አንዳንዴ «ለወገኔ ይጠቅማል» በሚል አላስፈላጊና ከንቱ አሳብ ውስጥ ሊያልፍ መቻሉ ሌላው ችግር ነው። ከዚህም የተነሣ፡—

- በአድልዎ፥ በዘር፥ በቋንቋ፥ በመቀራረብ፥ ወዘተ… መወሰድ ይፈጥርበታል። ከዚህም የተነሣ

- ሥጋዊነትን ማንጸባረቅና ማዘውተር የአገልጋዩ ችግሮች ይሆናሉ።

❖ እንዲህ ዓይነቱ ሕመም ሲገዳደረን በራእይ 5፡10 ላይ ያለውን የጌታን ቃል በማሰብ የመጣብንን ተግዳሮት መቃወም ይኖርብናል።

7. ያለ አግባብ አገልግሎትን በማብዛት ቤተሰቡን ወይም ትዳሩን የመዘንጋት ችግር ሊከሰትበትም ይችላል።

❖ በ1ኛ ጢሞ. 3፡4 ና 5 ላይ የተገለጠውን አሳብ ልብ ማለት ይጠበቅብናል።

8. አገልጋይ በአገልግሎቱ ስኬት ምክንያት በውስጡ የሚፈጠር ችግር ይኖርበታል።

አገልጋዩ በአገልግሎቱ ስኬት ሲገጥመው በጥንቃቄ ካልተመላለሰና በስኬቱ ላይ ባለማተኮር ካላገለገለ አደገኛ ችግር ነው።

እነዚህን ከመሳሰሉት ችግሮች የተነሣ በሕይወቱ ውስጥ ሳይታወቀው ከጸሎት፥ ከቃሉ ጥናትና ከራእይ መቀበያ መሠዊያው የመራቅ ሁኔታ ሊፈጠርበት ይችላል።

አገልግሎት በጌታ ጥሪና ጸጋ ብቻ የሚገኝ መሆኑን የአገልጋዩ መዘንጋት ከሚያስከትላቸው ችግሮች ከብዙ በጥቂቱ፡—

- መኩራራት፥ በራስ ያለአግባብ መተማመንና ራስን ለማሳየት መጣር፥ ራስን ማጉላት፥ ከዚህም ሲያልፍ አብረውት የሚያገለግሉትን መናቅና ማቃለል ይጀምራል (2ኛ ዜና 26፡16) (በተጨማሪም ሉቃስ 18፡9—14ን ይመልከቱ።)

- ራስን ምንም እንደማይሳሳትና እንደማይወድቅ የመገመት ችግር፥

- ራስን ከሌላው በጣም የተሻለ አድርጎ የመቁጠር ችግር

- የእግዚአብሔርን ክብር የመሻት ችግር ሁሉ ይፈጠሩበታል።

❖ ለዚህ ችግር ትልቅ መፍትሔ የሚመስለኝ ልብን መጠበቅ ነው።

9. አገልጋይ ስለ ገንዘብ ያለው (የሚኖረው) አስተሳሰቡ ሊበላሽበትና ፈተናም ሊሆንበት ይችላል። (ዕብ. 13፡5፤ 2ኛ ተሰሎ. 3፡7-13፤ 1ኛ ጢሞ. 6፡10፤ ሕዝ. 34፡1-3)።

በአገልጋይ ሕይወት ዙሪያ የገንዘብ ጉዳይ ትልቅ ችግር ነው።

❖ አገልጋይ ገንዘብን መውደድ አደጋው የከፋ መሆኑንና ለሌላም ጌታ ስግደት የመጀመር ያህል መሆኑን ተገንዝቦ መመለስ ይገባዋል።

## ማጠቃለያ

አገልጋይ እንደ ልዩ ፍጥረት ሊቆጠርና ሊገመት የሚገባው አካል አይደለም። ይልቁንም እንደ ማንኛውም ሰው በልዩ ልዩ ምክንያት ፈታኝና አስቸጋሪ ነገሮች ሊገጥሙት እንደሚችሉ በማሰብ ሊታዘንለት ይገባል። በአንጻሩም የሚቻለውን የሚቻለውን ያህል ጥንቃቄ እንደሚያስፈልገው ለእራሱ መማርና አማኞች ሁሉ በጸሎታቸው ሊደግፉት እንደሚገባ ማሳወቅ ይጠበቅበታል።

ለ) በአገልጋዩ ዙሪያ ከሌሎች የሚፈጠሩበት ችግሮች

መግቢያ፡-

አገልጋይ በአገልግሎት ዘመኑ ውስጥ አንዳንድ ጊዜ ከሚያገለግላቸው ወይም በዙሪያው ከሚገኙ ሰዎች መንፈሱን የሚጎዱና የሚያደክሙ ንግግሮች ወይም ድርጊቶች ሊያጋጥሙት እንደሚችሉ መረዳት አለበት። በዚህ ዓይነት ፈተና ከቆሙበት የወደቁና ከታዩበት የጠፉ ጥቂት አይመስሉኝም። ስለዚህ አገልጋይ እንዲህ ያለ አስቸጋሪ ገጠመኝ ሊጋረጥበት እንደሚችል በመረዳት ሊያገለግል ይገባል።

ከችግሮቹ ጥቂቶቹን ብናነሣ፡-

1. ለእግዚአብሔር ክብር ይሆናል ብሎ በሚያደርጋቸው ጉዳዮች ጣልቃ በመግባትና በማንቋሸሽ ተስፋ ለማስቆረጥ የሚደረጉ ትግሎች ይደቀኑበታል (ዘኁ. 12፡1-3፤ 16፡3)።

2. ሌላው ከሚያገለግላቸው ወይም ካገለገላቸው ወገኖች የጠበቀውን አጥጋቢ ለውጥና ውጤት አለማየቱ ለአገልጋዩ ሌላ ችግር ነው (1ኛ ሳሙ. 12፡1-25፤ ዘኁ. 14፡4-10)።

3. በመጨረሻ አገልጋዩ በሚያገለግላቸው አማካኝነት ራእዩን እንኳ የሚያስጥል ሁኔታ ሊፈጠርበትና ችግር ሊሆንበት መቻሉ ነው (ዘጸ. 32፡8፡19)። ይኸውም፥ የእስራኤል ሕዝብ ሙሴ ጽላቱን እንዲጥልና እንዲሰብር ያደረጉትን ያህል ማለት ነው።

❖ አገልጋይ መዘንጋት የሌለበት የእግዚአብሔር ሕዝብ እንኳን አገልጋዩን አምላኩንም እንኳ የሚያሳዝንና የሚያስቆጣ ሕዝብ መሆኑን ነው። እግዚአብሔር በዘኍልቊ ላይ ብዙ ስፍራ «አስቆጡኝ፥ አስቆጡኝ» ሲል እናነባለን።

## ማጠቃለያ፤

ቀደም ብሎ እንዳየነው አገልጋይ በግል ውስጣዊ እርሱነቱ ይሁን ከውጭ ከሚገኙት አስቸጋሪ ገጠመኞች ችግሮች ሊፈጠሩበት እንደሚችሉ ማወቅና ማመን ለሁሉም ግልጽ እንዲሆን ይረዳዋል። የአገልግሎትን አጨራረስ ለማሳመር በጸሎት ኃይል ዝግጅትና ትግል ማድረግ እንደሚጠበቅበት ለእያንዳንዱ ይህ ሥልጠና ያስገነዝባል።

## መደምደሚያ

«ነገር ግን ይህ ምሥጢር ለእኔ መገለጡ ፍቺው ለንጉሡ ይታወቅ ዘንድ፥ አንተም የልብህን አሳብ ታውቅ ዘንድ ነው እንጂ በዚህ ዓለም ካሉ ሰዎች ይልቅ በጥበብ ስለበለጥሁ አይደለም» (ዳን. 2፡30)። የዚህ ትምህርታዊ ሥልጠና አዘጋጅ አሳብም ከዚህ ጥቅስ አባባል የተለየ አይደለም።

በዚህች ትንሽ ጽሑፍ ውስጥ የተላለፉትን አጫጭር መልእክቶች ለመገንዘብ የቻልን ይመስለኛል። እንዲህ ከሆነ እነዚህን መሠረታዊ ነጥቦች መቀበል ብቻ ሳይሆን፥ እንደ ዱላ ቅብብሎሽ እኛም የዚህን ጽሑፍ መልእክቶች እንደ ታማኝ መልእክተኛ በሕይወታችንና በአገልግሎታችን በመለማመድ ለሌሎችም በማቀበል፥ በተለይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአገልግሎት ዙሪያ ብቃት ያላቸው አገልጋዮች እንዲበራከቱ ትልቅ መንፈሳዊ ኃላፊነትና አደራ ያለብን መሆኑን አጥብቄ አሳስባለሁ።

«ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ።» (2ኛ ጢሞ. 2፡2)።

ጌታ የተባረከ ይሁን!

# የትምህርት ዘጠኝ

## የሙከራ (የመወያያ) ጥያቄዎች

❖ ለአግሪጳም፡- «በጌታ የተቀበልኸውን አገልግሎት እንድትፈጽመው ተጠንቀቅ በሉልኝ» (ቆላ. 4፡17።)

1. አገልጋይ እንዴት ለችግር ሊጋለጥ ይችላል?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

2. በተለይ በአገልጋይ የግል ሕይወት ከሚፈጠሩ ችግሮች ጥቂቶቹን ግለጽ።

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

3. አገልጋይን ውጫዊ ችግር ሆነው ከሚፈትኑት ጥቂቶቹን ጻፍ።

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

4. በተጨማሪ በአንተ ዕይታ ችግር (ፈተና) የምትላቸውን አብራራ።

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

# ትምህርት አሥር

# አ ገ ል ጋ ይ ና ጊ ዜ ው

**ዓላማ:-** የአንድ አገልጋይ ትጋት የሚለካው ጊዜውን በአግባቡ መጠቀም በመቻሉ ጭምር መሆኑን ለማሳሰብ ነው::

**መግቢያ:-** ሁላችንም እንደምንረዳው በአገር፣ በማኅበረሰብና በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ሁሉ በርካታ ተሐድሶ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች እንዳሉ የተረጋገጠ ሲሆን፣ ከእነዚህ ዋና ዋና ጉዳዮች አንዱ የጊዜ አጠቃቀማችን ጉዳይ ነው::

ይህንን አንዳንድ ሰዎች ጊዜያቸውን ያለምንም የተጨበጠ ነገር አባክነው እንደሚጨርሱት ለመግለጽ የተጠቀሙበት አባባል ቢያስደንቀኝ አስነበብኳችሁ:- "አንዳንድ ሰዎች እንደማይሞቱ ሆነው በጊዜያቸው ሳይጠቀሙ ይኖሩና እንዳልኖሩ ሆነው ያለ መታሰቢያ ይሞታሉ::" ይኋል::

በመሠረቱ መታወስ ያለበት በዓለም ውስጥ ያለው እንቅስቃሴ ሁሉ በጊዜ ውስጥ የተካተተ መሆኑ ነው:: ጊዜ ለሰው ሕይወት ህልውና መከበር እጅግ ወሳኝ መሆኑ ቅንጣት ያህል አያጠራጥርም:: የአገራችን፣ የቤተ ክርስቲያን በምድራዊና በመንፈሳዊ ሁኔታዎች ሁሉ በሚገባ ያለማደጋችንና ያለመለወጣችን ምክንያቶች ብዙና ብዙ ቢባልላቸውም፣ ያ እንዳለ ሆኖ፣ ዋና ከሚሆኑት ችግሮች መካከል የጊዜ አጠቃቀም ችግር አንጋፋው ሳይሆን አይቀርም::

ስለ ጥሩ የጊዜ አጠቃቀም (Time management) የሚያስተምሩ ሰዎች ማኅበረሰባችን ምስቅልቅል ባለ ባህል ውስጥ ስለሚንቀሳቀስ ለጊዜ መበላሸት ይህን ያህል የማይቆረቆረው ስለ መሆኑ ከመጠቆም አልተቆጠቡም:: የእኛ አስቸጋሪ ልምድ ከልክ ባለፈ በሰበብ ባስባቡ ቁጭ ብሎ በማውራትና በመቀለድ ጊዜን ማባከን፣ በጊዜያቸው በትጋት የሚጠቀሙትንም ቢሆን ከማበረታታትና ምሳሌነታቸውን አድንቆ ከመከተል ይልቅ የመተቸት ባህል የተጠናወተው ስለሆነ አስተዳደጋችን ለእድገት ጠር መሆኑ በሁሉ የተረጋገጠ ነው::

- ይህ ታዲያ ሊታረም የሚገባውና ትግል የሚጠይቅ ስለሆነ ይህን ትምህርት የትግሉ አንድ ምዕራፍ እናድርገው::

ንባብ:- ዮሐንስ ወንጌል 9:1-7

"ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባኛል፤ ማንም ሊሠራ የማይችልባት ሌሊት ትመጣለች::"

- ❖ እርሱ ዘላለማዊ ስለሆነ እግዚአብሔር አምላካችንን ስለ ጊዜ ልንጠይቀው አንችልም:: ይሁን እንጂ፣ እርሱ በጊዜ መሥራትንና በጊዜ ማረፍን ለምሳሌ እንዲሆነን እንኳ ማሳየቱን መጽሐፍ ቅዱሳችን ከጅማሬው አንሥቶ ያስነብበናል::

- ❖ በዮሐንስ ወንጌል 9:4 ላይ የምናገኘውን አባባል ከተለያየ አንጻር ልንረዳው ብንችልም፣ በአጭሩ ግን:-

  1. የቀኑንና የማታውን ሁኔታ በማሳሰብ ሁሉም ነገር በጊዜ ውስጥ የተወሰነ መሆኑን ልብ ማለት አስፈላጊ መሆኑን የሚያሳስበን ነጥብ ሲሆን፤
  2. ጌታ እርሱ ራሱ በአይሁድ ፍርድ ለስቅላት ስለሚሰጥበት ስለ ጨለማው ሰዓት ጠቋሚ ከመሆኑ ባሻገር ጌታችን ኢየሱስ ምቹ ባልሆነ ጊዜ ውስጥ አልፎ ለእኛ ምቹ ጊዜ ሊተውልን መወሰኑን በማሰብ መሥራት ብልህነት መሆኑም አስተማሪ አባባል ይመስለኛል::

- ❖ የጊዜ ጉዳይ በበርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የምንማረው ሲሆን፣ ለሥራ ጊዜ፣ ለአገልግሎት ጊዜ፣ ለእረፍት ጊዜ፣ ወዘተ . . . እጅግ አስፈላጊ መሆኑ አያጠራጥርም:: (መክ. 3:1 ይመልከቱ::)

አሁን በመቀጠል በተለይ አገልጋይ ይበልጥ የጊዜ ውድነትና ክቡርነትን በመረዳት ጥሩ የጊዜ አጠቃቀምን (Time management) የሕይወቱ ክፋይ ያህል እንዲያስበው በንቃት እንዲከታተለው የሚከተሉትን መሠረታዊ ነጥቦች እንድናነሣ ግድ ይሆናል::

## ጊ ዜ ው ና  አ ገ ል ጋ ዩ

1. የጊዜን ክቡርነት የተረዱ አገልጋዮች የሚስተዋልባቸው ባሕርያት ምንድን ናቸው?

   1.1 ቀጠሮ አክባሪነት ይስተዋልባቸዋል:: ለራሳቸውና ለሌሎች ጊዜ የማይራሩ ቀልደኛ ሰዎች እንዲህ ሲሉ ይቀልዳሉ:- «ፀሐይ እስካልጠለቀች ቀጠሮአችን እንደ ተጠበቀ ነው::»

   - ❖ አንድ አገልጋይ በተለይ የአገልግሎቱንና ከሰዎች ጋር የሚኖረውን ቀጠሮ የማያከብር ከሆነ፣ ሰዎቹ ከሚኖራቸው ዕድሜ ላይ በሰዓታት፣ በደቂቃ የሆነ ያህል ሰርቆ የሰዎቹን የዕድሜ ቁጥር ለኪሳራ መዳረጉ መታወቅ አለበት::

* በሌላ አንጻር አገልጋዩ የጊዜን ክቡርነት በመረዳት ጥሩ ቀጠሮ አክባሪ ሆኖ ቢገኝ፣ ቢያንስ እነዚህ ሦስት ትላልቅ ነገሮች ይፈጠራሉ::

1.1.1. ከቀጠሮ አክባሪነት የተነሣ በቀጠሮ ሰጪውና በቀጠሮ ተቀባዩ ሕይወት ውስጥ ደስታን የሚፈጥር ይሆናል::

1.1.2. ቀጠሮ አክባሪዎቹን ሰዎች ቁም ነገረኛ የሚያስብላቸውን ሁኔታ ይፈጥራል፤ ለሌላውም ጊዜ አስተማማኝ ግንኙነት እንዲኖር መንገድ ያመቻቻል::

1.1.3. ጊዜ እንዳይባክን ጥሩ ምክንያት መሆንንና ሊሠራ የታሰበው ሥራ በወቅቱ እንዲሠራና ውጤታማ መሆን እንዲቻል በጎ አስተዋጽኦ ያደርጋል::

1.2. በጊዜ አጠቃቀም ጉዳይ ዙሪያ ንቁነት ይስተዋልባቸዋል::

* መዝሙረኛው በአንድ ስፍራ፣ «ለሞት እንዳልተኛ ዓይኖቼን አብራ ብሏል::»

* ሌላው አንድ የፈረንሳዮች አባባል ይታሰበኛል:- "ድሃ መሆን ከፈለግህ እስከ ሰባት ሰዓት ተኛ" ይላሉ:: በጊዜያቸው ዙሪያ ንቁ የሆኑና ጊዜም ራሱ መንፈሳዊ፣ ግላዊ፣ ማኅበራዊና ቤተሰባዊ ትልቅ አጀንዳ መሆኑን የተረዱት ቅዱሳን በንቃት መንዝረው ሊጠቀሙበት ፈልገው እግዚአብሔርን በዕድሜያቸው፣ በጊዜያቸው ዙሪያ አጥብቀው ሲማጠኑት:- "በእኛ ዘመን፣ በእኛ እድሜ ሥራህን ፈጽም"፣ "እድሜዬን፣ ዘመኔን ለሚረባ ዋጋ ላለው ነገር ተጠቀምበት::" እንደ ነበር ጸሎታቸው ከታሪካቸው እናጠናለን:: (መዝ. 27:4፤ ዕንባቆም 3:3 ይመልከቱ::)

* ስለዚህ የዛሬዎቹም ቅዱሳን ስለ ዘመናችን፣ ስለ ጊዜያችን ተጨናቂና ተቆርቋሪ፣ እንዲሁም የምንንገበገብለት ልንሆን እንዲ ቻል እንድንለው አልተመከርንም::

1.3. ጊዜያቸውን በአግባቡ ለመጠቀም ቅደም ተከተሉንም ለመቆጣጠር በጊዜ ዕቅድ የመንቀሳቀስ ዘይቤ ይስተዋልባቸዋል::

* ድንገተኛ ለሆነው የሚሰጡት ምላሽ

* ለቋሚ ሥራዎቻቸውና ጉዳዮቻቸው የሚሰጡት ምላሽ ፍጹም ግልጽና ግራ የማያጋባ መሆኑን፣ ቅድሚያ የሚሰጠውንና መከተል ያለበትን በየመስመሩ በማስኬድና ጊዜን በጥሩ ስልት በመጠቀም ብቃት ይታይባቸዋል::

❖ ከያዙት የጊዜ ዕቅድ ውጭ በቀላሉ ለገጠማቸው ሁሉ በመጠለፍ ተሸናፊ አይሆኑም:: በጊዜ መገኘትና በጊዜ መሥራት ያለበትን መሥራት ባህላቸው ያደረጉ ብልሆች ናቸው::

## II. ጊዜን አክባሪና ተጠቃሚ አገልጋዮች ምን ውጤት ይገጥማቸዋል?

### 2.1 የራሳቸውንና የሌሎችን ጊዜ ውጤታማ ለሆኑ ጉዳዮች ብቻ የማዋል ብቃት ይገጥማቸዋል::

❖ ጤናማና ትክክለኛ ጊዜ አጠቃቀም ውስጥ የተገኘ እድገትና ስኬቱ በራሱ ዙሪያ ብቻ የሚያልቅ በራሱ ውስጥ ብቻ የሚቀር ሳይሆን፣ ለትውልድ የሚሸጋገር ሐብት ሆኖ ይጓዛል::

❖ ጌታም እኮ ያስተማረን በቀኑ መሠራት ያለበት ሥራ ከተሠራ፣ ጊዜን በጊዜው ከተጠቀምንበት፣ የእርሱኑ ለአብ ክብር እንደ ነበር፣ የእኛኑም እንዲሁ እንዲሆን የሚጋብዘን ነው::

❖ እኛም እንደ ብልህ ክርስቲያን፣ አገልጋይ የሥራውን ለሥራ፣ የእረፍቱንም ጊዜ ለእረፍት መጠቀሙን ከአምላካችን የምንማረው ነው:: (ዘፍ. 2:2 ይመልከቱ:)

❖ ሌላው መታወቅ ያለበት ትክክለኛ እድገትና ስኬት ማለት የሚቻለው በትክክለኛ የጊዜ አጠቃቀም ውስጥ የተገኘ እድገት፣ ውጤት እስከሆነ መሆኑን ቆም ብለን እናስብ:: በሌላ ጫፍ የተዛባ የሠራተኛነት አካሄድ ከብዙ አንጻሩ ቀውስ እንደሚያስከትል በማመን ፈጠን ብሎ ማረም ይገባል:: የሕይወትን ሩጫ ወደ አንድ ጫፍ ብቻ አስሩጦ መጨረስ ክፉ አዝማሚያ ነው::

"ጊዜያቸውን ሁሉ ገንዘብን ለማግኘት ሲሉ ይሠሩና ጤንነታቸውን ያቃውሳሉ የኋላ ኋላ ያገኙትን ገንዘብ ሁሉ ለሐኪም ይሰጣሉ::" (ሆዶስ መጽሔት)

### 2.2. ጊዜን በአግባቡ የሚጠቀሙና የሚያከብሩ የአዳዲስ ጠቃሚ ግኝቶች ባለቤት የመሆን ዕድል ይገጥማቸዋል::

❖ እነዚህ ጊዜያቸውን አክባሪና ተጠቃሚ ሰዎች ወይም አገልጋዮች በየትኛውም በተሰማሩበት መስክ የአዳዲስ ሥራዎች ባለቤት ለመሆን እጅግም አይቸገሩም:: ችግር ቢሆን ጊዜን በጊዜው አለመጠቀም ነው፤ የአዳዲስ ፈጠራ ባለቤት ለመሆን አለመሥራት በደል ነው::

ምሳሌ:- ጥንት ያኔ ድሮ ስዊዞች የሮመርን ሰዓት መሥራት እንደ ቻሉ ጉድ እንደ ተባለላቸው፣ ነገር ግን ምንም ሳይቸግራቸው በፊታቸው ያለውን ጊዜ ለአዳዲስ ሥራዎች ዐቅዶ ከመነሣት ይልቅ የሠሩትን ሮመር የመጨረሻና የሥልጣኔ ቁንጮ ከማድረጋቸውና ከጥረት ከመቆጠባቸው የተነሣ የሰዓትን ሥራ በአዳዲስ ሥልጣኔ መቀጠል አለመቻላቸው እንዲያውም ያን ሥልጣኔ ሌሎች እንደ ነጠቋቸው ይነገራል።

እርግጥ አንዳንድ ጊዜ ባለፈው እየተኩራራን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የነገውን ያለ ልክ ናፋቂ ሆነን ከሁለት ያጣ እንዲሉ ገመዱ ያጥራል።

«ለነገና ለወደፊቱ የበለጠ ትኩረት በመስጠት የዛሬው ጊዜያቸውን ለሚያባክኑ ዛሬም ሆነ ነገ በቅጡ ሳይሠሩበት ያልፍባቸዋል።» (ሆዶስ መጽሔት)

- ❖ ስለዚህ የአዳዲስ ጠቃሚ ነገሮች ባለቤት ለመሆን ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ጠቀሜታው ይህ ነው እንደማይባል እርግጠኛ እንሁን።

2.3. ጊዜን አክባሪና ተጠቃሚ አገልጋዮች ያላቸውን ጊዜ ሁሉ ለራሳቸውና ለሌሎችም ጥቅም የመጠበቅና የመጠቀም ሁኔታ ይስተዋልባቸዋል።

- ❖ አዋቂዎቹ ስለ ጊዜ የሚሉትን እናስታውስ፤ "ትናንት ሠርተህበት ቢሆን አልፏልና እርሳው፣ አትመካበትም፣ ነገ ምናልባት የአንተ አይሆንምና ያለ አግባብ አትጨነቅለት፣ ዛሬን ግን ፈጣሪህ በእጅህ ያኖረልህ ገንዘብህ ስለሆነ ተጠቀምበት" ይላሉ።
- ❖ ሰው በተሰጠው ሳይጠቀም ሌላ የሚያባክነውን ጊዜ ጨምርልኝ ብሎ አምላኩን መለመን ምን ይሠራል?
- ❖ በተለይ የአንድ ክርስቲያን ጊዜ የአምላኩ የእግዚአብሔር አንጡራ ሐብት እንደ ሆነ፣ ለእርሱም በአደራ የተሰጠው እንደ ሆነ በመገንዘብ ከማንኛውም ሰው በተሻለ ደቂቃዎች እንኳ ያለአግባብ እንዳይባክኑ ጥንቃቄ ሊያደርግላቸው እንጂ፣ እንቅስቃሴዎቹን ሁሉ ለበኋላና ለነገ እየገፊተረ በሚያገኘው ነገ መተማመኑን አቁም የዕለቱን ለዕለቱ ማከናወንን ልምዱና ባህሉ ያድርግ የሚለው በጎ ምክር እውነትነት አለው።

"አንዳንድ ሰዎች እንደማይሞቱ በጊዜያቸው ሳይጠቀሙ ይኖሩና እንዳልኖሩ ሆነው ያለምንም መታሰቢያ ይሞታሉ።" (ያልታወቀ)

- ❖ እንደ እውነቱ ከሆነ በርካታ ጠቃሚና ለሰዎችም ባለ ውለታ፣ ለፈጣሪያቸውም ክብር መገለጫ የሚሆኑት ሰዎች የጊዜን ክቡርነት የተረዱና ጊዜያቸውን በሚገባ ተጠቃሚዎቹ ለመሆናቸው የሚጠራጠር አይኖርም።

- ❖ ደግሞም ልበ ሙሉነትና የመንፈስ እርካታ ከምንም ዓይነት የሕሊና ክስ ነጻነት ያላቸው እነዚሁ የጊዜ ውድነት የገባቸው እንጂ፣ ጌታን ተቀብያለሁ፣ ጌታን አገለግላለሁ ባዮች ብቻ ሊሆኑ አይችሉም። ምክንያቱም ጌታን መቀበልና ጌታን ማገልገል ጌታ የሰጠንን እድሜ በሚገባ ሁኔታ በሚገባው ጊዜ መንዝሮ በመጠቀም ውስጥ ጭምር እንጂ፣ የተሰጠንን ማባከንና ማበላሸት ከጌታ ጋር መሆናችንን አይተረጉምም።

III. የጊዜን ክቡርነት የማይረዱና የማይጠቀሙበት ሰዎች የሚስተዋልባቸው ባሕርያት:-

- ❖ ቀደም ሲል ስለ ጥሩ የጊዜ አጠቃቀም (Time Management) የተጠቀሱት አስተማሪዎች በጊዜ አጠቃቀም ዙሪያ ትክክለኛ የሆኑትን ባሕርያትና የሚያስከትሉትን ለውጥ ብቻም ሳይሆን፣ በጊዜያቸው ላይ ጥፋት የሚያደርሱ ሰዎችን ባሕርያትንና የሚገጥሟቸውን ክፉ ውጤቶች እንደ ጠቆሙን እንመለከታለን።

እነዚህ ጊዜን በሚገባ የማይጠቀሙና ይልቁን የሚያባክኑ ሰዎች ሕይወታቸውና የሕይወታቸውም ውጤት ምን ያህል አሳፋሪና አሳዛኝ መሆኑን ባለሙያዎቹ ካገኙት ጥናት ያካፈሉ ሲሆን፣ ልብ ያለ እውነቱን ልብ ይላል።

3.1 ጊዜያቸውን በመባከንና በማባከን፣ ይሄንንም ያንንም ያዝ ለቀቅ የማድረግ ነገር ሲያጠቃቸው ይስተዋላል።

- ❖ እዚህ ገባሁ፣ እዚያ ወጣሁ፤ ይህን አስቤ ነበር፣ አሁን ደግሞ ይህኛውን አሰብኩ፤ እዚያ ሄድኩ፣ ነገ ደግሞ እዚያ ልሄድ ነው በመሳሰሉት በማይጨበጡና ለውጥ በማይታይባቸው ንግግሮች ብቻ የተሞሉ የአፍ ሪፖርተሮች በመሆናቸው፣ ሳይወዱ ለውሸት የተጋለጡ ይሆኑና፣ ባልነበሩበት እንደ ነበሩ፣ ባልደረሱበት ጊዜ እንደ ደረሱ፣ ያልሠሩትን እንደ ሠሩ ሆነው ጊዜያቸውን (ዘመናቸውን) ያቃጥላሉ።

- ❖ አንዳንዴ እንደ እነዚህ ዓይነት ሰዎች ሳንሆን አንቀርም በሥራ በጣም መወጠራችንን («Busy» መሆናችንን) የምናስተጋባው። በምንሠራባቸውና በማንሠራባቸው ጊዜያት ዙሪያ በተለያዩ ጊዜያት ጥናቶች ቀርበዋል።

በተለይ በእኛ አገር በ20 ዓመታት ንጹሕ የሥራ ዕድሜ ውስጥ አንድ ሰው ልቡ እስኪጠፋ እንኳን ሠራ ቢባል ከ2 እስከ 5 ዓመታት እንጂ ከዚያ በላይ ሊሆን እንደማይችልና የቀሩት 15 ዓመታት እሠራለሁ፣ ይሠራል እየተባለ የሚበላሹ የማይሠራባቸው ጊዜያት መሆናቸውን አጥኚ ዎቹ ይጠቁማሉ:: "ምናልባትም በብዛት የተጫወትን ባቸውን ጊዜያት ሁሉ ከቁም ነገርና ከሥራ አንጻር ቆጥረናቸው ይሆናል" ይላሉ::

3.2 ጊዜያቸውን በቸልተኝነትና በዝንጉነት የማበላሸት ነገር ሲያጠቃቸው ይስተዋላል::

- የጊዜ አጠቃቀም መምህራን:- "ቸልተኝነት፣ ዝንጉነትና ሁሉን ጉዳይ ለነገ የማሳደር ልምድ ከሰይጣን የሚወረስ ጊዜያችንን ማባከኚያ ወይም ጊዜን የመግደያ ክፉ መሣሪያ ነው" ይላሉ::
- አንዳንዴ እንዲያው በከንቱ ለሚጠፋው ጊዜያችን ምንም ያህል ጸጸት ሳይሰማን መቅረቱ፣ ምን ያህል ዘግናኝና አደጋም እያንዣበበብን መሆኑ ልብ አለማለት ክፉ ድንዛዜ እንዳጠቃን ምልክት ነው::
- «አይ! እርሱ፣ እርሷ፣ እነርሱ ያረፍዳሉ እንጂ በፍጹም አይቀሩም» መባል ትልቅ ስድብ አይመስለንም?

3.3. ከክፉው የጊዜ አጠቃቀማቸው የተነሣ ደካማነትና ፍሬቢስነት ሲያጠቃቸው ይስተዋላል::

- አጥኚዎቹ:- "እንደ እነዚህ ዓይነት ሰዎች ከራሳቸው አልፈው ሌላውንም እንኳ እነርሱ በተጠመዱበት የጊዜ አባካኝነት ወጥመዳቸው ለማጥመድ በወሬ፣ በስንፍና ደካማና ፍሬ ቢስ ለማድረግ አውቀውም ሳያውቁም ደፋ ቀና የሚሉ እንደ ሆኑ፣ ከዚያም ባለፈ ስለ ጊዜ በአብዛኛው ተጠያቂነት የጊዜ ብክነት ባለ ዕዳነት ክስ በሕሊናቸው ይሰማቸዋል" ይላሉ::
- በተለይ አንዳንድ አባባሎች እውነትነታቸውን እኛ አበሾቹ ልብ ሳንል የምንቀር አይመስለኝም:: "ወሬ ወዳዶቹ:- ቡና ልባቸውን፣ ሐሜት ነፍሳቸውን፣ ሰይጣን ጊዜያቸውን ልጦ ለአደጋ ይጋለጣሉ::" ይባላል::

3.4. ለቁም ነገር ከሚጠቀሙበት ጊዜያቸው ይልቅ በፌዝና በቀልድ ጊዜያቸውን የማጥፋት ነገር ሲያጠቃቸው ይስተዋላል::

❖ በተለይ የአገራችንን ወጣት ትውልድ የሚስበውና የሚገፋው በቁም ነገር ጊዜን የመጠቀም ሳይሆን፣ በአብዛኛው በፌዝ ጊዜውን መግደል ነው ማለት ይቻላል:: ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሳችንን በጥንቃቄ ስናጠና፣ እግዚአብሔር በየትኛውም ዘመን በታላቅ ኃይሉ የተጠቀመባቸው 99% ያህል ማለት ይቻላል ትላልቅ ቁም ነገሮች የተከናወኑት በወጣቶች መሆኑ ያለጥርጥር የተረጋገጠ ነውና፣ ክርስቲያን ወጣቶች በተለይ በጊዜ አጠቃቀም ዙሪያ ልብ ማለት ይጠበቅባቸዋል::

ወደ እኛ ዘመንና አገር ስንመለስ፣ ከቁም ነገር መንደር በርግማን የተባረረ ይመስል በተለይ አብዛኛው ወጣት ጊዜውን የሚፈጀው በእንቶ ፈንቶ ቀልድ መሆኑ አሳፋሪና አሳዛኝ ብቻ ሳይሆን፣ ካልነቃንበት አስጊም ነው::

IV. የጊዜን ክቡርነትና ውድነት በመረዳት በአግባቡ ለመጠቀም የሚረዱን ሐሳቦች ምንድን ናቸው?

❖ በዚህ የጊዜ አጠቃቀም ጉዳይ ዙሪያ ማንም ከማንም የተሻለ ጥራት ያለው ነው ብሎ በእኛ በአበሾቹ መካከል በቂ ምስክርነት መስጠት አፌ ሙሉ የሚያደርግ አቅም መኖሩ አጠራጣሪ ነው:: ይሁን እንጂ፣ ዛሬ የትናንቱን በጊዜያችን ላይ የፈጸምነውን በደል ሁሉ ከአሁኑ ደቂቃ አንሥቶ ለመበቀል መነሣሣት እንዳለብን ማወቅ ድንቅ ንቃት ይመስለኛል:: ስለዚህ ለዚህ መነሣሣት የሚረዱንን መሠረታዊ ጥቆማዎች እንጠቀምባቸው::

4.1. ግለሰቡ ከሁሉ አስቀድሞ የሕይወቱን፣ የሥራውን፣ የነገሮቹን ሁሉ ቀዳሚና ተከታዩን የዕለት ተዕለት የጊዜ በጀት ዕቅድ መሥራትን ባህሉ ማድረግን መጀመር ይኖርበታል::

❖ ይህ እስኪለመድ ትልቅ ፈተና መሆኑ አይዘነጋም:: አንዳንድ ጊዜ ታዲያ ድንገተኛ ሆነው ቅድሚያ የሚጠይቁን ሁኔታዎች ታሳቢ መደረግ አለባቸው:: በተረፈ ግን፣ በተቻለ አቅም ለጥሩ የጊዜ አጠቃቀምና ለጊዜ ዕቅዳችን ተገዢ በመሆን ደስተኛ መሆንን እንለማመድ::

4.2. ሁሉንም እኛ ብቻ ለማከናወን ከምናደርገው ውጥረት መውጣት መቻል ግድ መሆኑን እንወቅ፣ እናድርገውም::

❖ አንዳንዴ ይላሉ «ሁሉን እኔ ብቻ ልሥራው ባይ ሰው ሰው ስለ ጠፋ ሳይሆን «ክሬዲቱን» ወይም መሞገሱንና መወደሱን ለራሱ ብቻ ለማድረግ ናፋቂ ስለሆነ እራስ ወዳድነት ስለሚያጠቃውም ነው::» ይባላል::

4.3 ቢሠራ ፍሬያማ ሊያደርግ በሚያስችል ነገር ላይ ብቻ የተለየ ትኩረትና ጊዜ መስጠትን ልምድ ማድረግ፣

❖ ሁሉን ስለ ሠራን በሁሉ ውጤታማ ልንሆን እንደማንችል እርግጠኛ በመሆን፣ ዋጋ ባለውና ለሌላው በሚበጅ ሥራ ላይ ጊዜን ማሳለፍን ዋና ጉዳይ ማድረግ ወሳኝ ነው::

4.4. የግለሰቡ አቅምና ጊዜ በሚፈቅድለት ሥራ ላይ ለመሰማራት የጊዜን ምቹነትና የአቅምን ልክ ማወቅ፣

❖ ምን ጊዜም ከአቅማችንና ከጊዜያችን ልክ አልፈን በመወጣጠር ከተንቀሳቀስን፣ እራሳችንን ከማጣበብ ያለፈ እኛንም ይሁን ሌላውን የማያረካ ተግባር ከመፈጸም የዘለለ ፋይዳ ስለማይኖረው፣ ባለን ጊዜና አቅም መጠን መንቀሳቀሱን እንርሳው::

4.5. በየዕለቱ የጊዜ አጠቃቀማችን ሁኔታ እንዴት እንደ ነበር መገምገምን ባህላችን ማድረግ፣

❖ ሁላችንም እንደምናውቀው፣ በማንኛውም እንቅስቃሴ አንጻር ግምገማን ማካሄድ የሚታመንበትና በጣም የሚበረታታ ጉዳይ ነው:: ምክንያቱም ጉድለቶቻችንም ሆኑ ስኬቶቻችን ሊለኩ የሚችሉት በጊዜው የጊዜ አጠቃቀማችንን የገመገምን እንደ ሆነ ነው:: እውነተኛ ሆነን እራሳችንን መውቀስ በሚገባን ለመውቀስ፣ እራሳችንን ማድነቅም ቢኖርብን ለማድነቅና ለነገ የተሻለ ለማሰብ ከምንም በላይ የጊዜ ባለቤት የሆነውን አምላካችንን እግዚአብሔርን ለማመስገን የጊዜ አጠቃቀማችን መገምገም አለበት::

# ማጠቃለያ:-

በተለይ እኛ በእግዚአብሔር ቤት የምናገለግል ክርስቲያኖች ሁላችን እግዚአብሔር ለሰጠን ጊዜ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት እስከ አሁንም በማኅበረሰቡ ዘንድ፣ በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ፣ በቤታችን ውስጥ፣ በግላችንም ጭምር እንዴት እየተጠቀምንበት ዛሬን እንደ ደረስን እያስታወስን በጊዜያችን ጥሩ ተጠቃሚ ፍሬያማም ትውልድ እንሁን:: የምናውቀውን የተበላሸና የሚበላሽ የጊዜን አጠቃቀም ተጋፋጭና ሰባሪ ሆኖ ለመገኘት መጣጣር እንጂ የተሰጠንን የጊዜ ሀብት በዋዛ አባካኝ ፍሬ ቢስ ሆኖ ከመንቀሳቀስ ጌታ እንዲያስመልጠን መማጠን የጊዜያችንም የትውልዳችንም ተጠያቂ እንዳንሆን ንቁ መንፈስ እግዚአብሔር ይስጠን! ትምህርቱንም በዘመናችን እንጠቀምበት!!

“ዳዊትም በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን አሳብ ካገለገለ በኋላ አንቀላፋ::”

(ሐዋ. 13:36)

# የትምህርት አሥር
## የሙከራ (የመወያያ) ጥያቄዎች

1. ጊዜ ምንድን ነው?

2. የጊዜን ክቡርነት የተረዱ አገልጋዮችን ባሕርያት አብራራ::

3. ጊዜን አክባሪና ተጠቃሚ አገልጋዮች ምን ውጤት ይገጥማቸዋል?

4. አንተስ ጊዜህን በምን መልክ እየተጠቀምክበት ነው?

# የግል ምስክርነት

በዚህ አገልጋዩን ለአገልግሎቱ በሚለው ትምህርት ለእኔ ካሳለፍኩት የአገልግሎት ዘመኔ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖቼን መዝኜ እንድመለከትና ዋጋዬን በመተመን ጌታ እስኪመጣ ወይንም እኔ ወደ ጌታ እስከምሄድ ድረስ ለወደፊቱ ጌታ በሚያሰማራኝ በማንኛውም የአገልግሎት መስክ ክርስቶስ ሁኔታዎች እንደተፈለገ በማይሆኑበትና በሚሆኑበት ጊዜ ሁሉ ችግሩን ችሎ (ታግሶ) እንዳገለገለ እጅግ በጥንቃቄና በትጋት ከሚጠበቅብኝ በላይ ዋጋን ለመክፈል የጌታን ጸጋ እና እርዳታ በመጠየቅ ለማገልገል እንድነሣሣና እንድዘጋጅም ለመወሰን እንድችል እጅግ በጣም ጠቅሞኛል። ይኸውም «አስተዋይ አገልጋይ በንጉሥ ዘንድ ይወደዳል፤ በሚያሳፍር ላይ ግን ቁጣው ይሆናል» ተብሎ በምሳሌ 14፡35 እንደተጻፈው፥ በተጨማሪም «የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ እኔም ባለሁበት አገልጋዬ ደግሞ በዚያ ይሆናል፥ የሚያገለግለኝም ቢኖር አብ ያከብረዋል» ተብሎ በዮሐንስ 12፡26 እንደ ተጻፈው ማለት ነው።

❖ የተከበራችሁ የእግዚአብሔር ልጆች፥ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ትምህርቱን በሚመለከት አጠር ያለ መግለጫ አቀርባለሁ።

## አገልጋዩን ለአገልግሎቱ

ይህ ትምህርት በእኔ መረዳት በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡—

1ኛ. አገልግሎትን በአዲስ ለሚጀምሩ ያላወቁትን ተምረው እንዲነሣሡና ወስነው ጽኑ አገልጋዮች እንዲሆኑ ያደርጋል።

2ኛ. በማገልገል ላይ ላሉት ደግሞ ጉድለታቸውን እንደ መሥታወት አጥርቶ በማሳየት እንዲስተካከሉ፥ በበለጠ በርትተው እንዲተጉ እና እንዲተከሉም እጅግ ጠቃሚ ነው።

3ኛ. አገልግሎታቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ላቋረጡ እጅግ የጎበጠውን አቃንቶ በማደስ ወደፊት ለሚጀምሩት አገልግሎት በአዲስ አእምሮ እና መንፈስ ጸንተው ለማገልገል እንዲነሣሡና መወሰን እንዲችሉ እጅግ የሚረዳ ነው።

አስቴር ጋረደው

የ3ኛው ዙር ሠልጣኝ

## አገልጋዩን ለአገልግሎቱ

አገልግሎት ምንድን ነው?
አሳቡ ምንድን ነው?
ምንን ይወክላል፥ ተግባሩስ ምንድን ነው?
መሠረት እንዳለው ይታወቃል ወይ?
ለሥራው ታማኝ ዋጋውን ከፋይ
በዓላማ' ሚከወን ነው አገልግሎት
ሠራተኛው ፍቅርን ምክንያት አድርጎት
ለእንጀራችን ሳንል ለዕለት ጥቅማችን
ለመባረክ ሳይሆን ስለተባረክን
ለምሳሌነት ነው አገልግሎታችን።
የምንሠራው እኮ የጌታን ሥራ ነው
ጌታ የተወልን ታላቅ አደራ ነው።
አገልግሎት ማለት የሁሉም እኩል ነው
ደረጃ የሌለው ሁሉም አንድ ዓይነት ነው።
በሕመም በረሃብ ደግሞም በስደት
ሊገታ አይችልም ይህ አገልግሎት።
ስንቶች ገብቶን ይሆን እንዲህ የመሆኑ
ልናስብ ይገባል ሳያልቅ ዘመኑ።
ጥሪን ተገንዝቦ ለሚሠራው ሰው
ሽልማት ያገኛል ከሚያሰማራው።
ልንሮጥ ልንሠራ ትጋትን ልንጨምር
ዘመኑ አሁን ነው ጌታን ልናስከብር
ዓላማችን ይሁን ጌታን ልናስከብር።

አረጋሽ ወ/ሚካኤል
የ3ኛው ዙር ሠልጣኝ

የዚህን ጽሑፍ ሥልጠናና ሌሎች የአገልግሎት ሥልጠናዎችን የምትሹ
በሚከተለው አድራሻ ልታገኙ ትችላላችሁ።
ወንጌላዊ አበበ ብርሃኑ
አቃቂ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን /ጅማ መንገድ/
የስልክ ቁጥር 20 05 03/ 49 32 48/ 49 08 48
የመ.ሣ.ቁጥር 13179
አዲስ አበባ

## በዝግጅት ላይ ያሉ ሌሎች የጸሐፊው ሥራዎች፣

- «የማይዳፈነው እሳት»: የማስተማሪያ መጽሐፍ
- «እያስተማራችኋቸው»: ለመምህሩ - ማሠልጠኛ መጽሐፍ